የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 26
ADDIS ABABA - 9th March, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፰/፲፱፻፺፪ ዓ·ም·
የእንስሳት ፡ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ............................ ገጽ ፩ሺ፪፻፷፪

## CONTENTS

Proclamation No. 198/2000
Animal, Animal Products and By-products Marketing Development Authority Establishment (Amendment) Proclamation .................... Page 1262

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፰/፲፱፻፺፪ ዓ·ም·
### የእንስሳት ፡ እንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣው ማሻሻያ አዋጅ

የእንስሳት ፡ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· __አጭር ርዕስ__

ይህ አዋጅ "የእንስሳት ፡ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፰/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

2· __ማሻሻያ__

የእንስሳት ፡ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፯/፲፱፻፺ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩· በአዋጁ ውስጥ "እንስሳት ፡ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን" የሚለው ስያሜ "የእንስሳት ገበያ ባለሥልጣን" በሚል ተተክቷል ።

፪· አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል ፤

"፩· "እንስሳት" ማለት የዳልጋ ከብት ፤ በግ ፤ ፍየል ፤ ግመል ፤ ዶሮ ፣ አሣማ ፤ ንብ እንዲሁም ባለሥልጣኑ ወደፊት "እንስሳት" ብሎ የሚሰይማቸውንና ለዚህ አዋጅ ዓላማ ሲባል በአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) እንደተገለጸው የእንስሳት ምርትና የእንስሳት ተዋጽኦን ይጨምራል ።

### PROCLAMATION NO. 198/2000
### A PROCLAMATION TO AMEND THE ANIMAL, ANIMAL PRODUCTS, AND BY–PRODUCTS MARKETING DEVELOPMENT AUTHORITY ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the proclamation provided for the establishment of Animal, Animal products and By-products Marketing Development Authority;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Animal, Animal products, and By-Products Marketing Development Authority Establishment (Amendment) Proclamation No. 198/2000."

2. *Amendment*

The proclamation provided for the Animal, Animal Products and By-products Marketing Development Authority Establishment Proclamation No. 117/1998 is hereby amended as follows:

1) The "Animal, Animal Products and By-Products Marketing Development Authority," referred in the proclamation is replaced by and, shall be referred to as the "Livestock Marketing Authority."
2) Sub-Article (1) of Article 2 of the proclamation is hereby deleted and replaced by the following new-Sub-Article (1):

"1) "Livestock" means Cattle, Sheep, Goat, Camel, Poultry, Pig, Bee and which the Authority may designate as "Livestock", and for the purpose of this proclamation shall include livestock products and by-products as defined under Article 2 Sub-Articles (2) and (3) of the proclamation;"

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· በአዋጁ አንቀጽ ፲ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ተጨምረዋል ፤

“፭ የባለሥልጣኑን ድርጅታዊ መዋቅርና የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል የባለሥልጣኑን ሙያተኛ ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል ፣ የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ በማውጣት ፣ መዋቅሩንና መመሪያውን ለመንግሥት በማቅረብ ያስጸድቃል ፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል ፤”

“፮· በሥራ አስኪያጁ የሚቀርበውን የመምሪያ ኃላፊዎችን ሹመትና ስንብት ያጸድቃል ።”

፬· የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፪/ለ/ ተተክቷል ፤

“ለ) ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሙያተኛ ሠራተኞች ይቀጥራል ፤ ያስተዳድራል ፤ ደመወዝና አበላቸውንም ይወስናል ፤ የባለሥልጣኑን ሌሎች ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል ፤ ያስተዳድራል ።

፫· <u>*አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ*</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



3) The following new Sub-Articles (5) and (6) are added under Article 10 of the proclamation.

“5) following the basic principles of the federal civil service laws, prepare and submit, to the government, the organizational structure and salary scale, a directive for the employment and administration of professional staff of the Authority, and follow up the implementation of same upon approval;”

“6) approve the appointment and dismissal of department heads proposed by the manager;”

4) Sub-Article 2(b) of Article 11 of the proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Sub-Article 2(b):

“b) Employ and administer the Professional staff of the Authority in accordance with directive approved by the government and other staff in accordance with the federal civil service iaws;”

3. *Effective Date*

This proclamation shall come into force as of the 9th day of March, 2000.

Done at Addis Ababa, this 9th day of March, 2000.

*NEGASO GIDADA (DR.)*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL*
*DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
*BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE*